በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን

# ቅርስን ከስብስብ ለማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጡትን ስብስቦች ለማስወገድ የተዘጋጀ መመሪያ

ቁጥር 763/2013

ሐምሌ 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

**መግቢያ**

በስብስብ ማእከል ውስጥ አንድ አይነት ቅርስ ከሚፈለገው ቁጥር በላይ ከሆነ ወይም ድገግሞሽ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም በትክክለኛ ቦታው ያልተቀመጠ ከሆነ ወደ ሚመለከታቸው ተቋማት በመስጠት ወይም በመለዋወጥ ከስብስብ ክፍሉ ማስወጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በጉዳታቸው ምክንያት መጠገን የማይችሉትን ፣በመበላሸታቸው የቅርስነት እሴታቸውን በማጣት ለሌሎች ቅርሶችና ሰዎች ደህንነት አደገኛ መሆናቸው ሲረጋገጥ አንድን ቅርስ ወይም ስብስቦችን ከቅርስ ስብስብ ማዕከል በቋሚነት ማስወገድ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ቅርስን ከስብስብ ማዛወርና ማስወገድ በተጠና ስርዓትና ግልፅነት ባለው አሰራር መከናወን ያለበት በመሆኑ፤

በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

### 1. አውጭው ባለሥልጣን

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ቅርስን ከስብስብ ለማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጡትን ስብስቦች ለማስወገድ የተዘጋጀ ረቂቅ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ ካልተሰጠው በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 3 የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም፡-

1. **ቅርስን ከስብስብ ማእከል ማዛወር፡-**

   እንደየስብስብ ማእከሉ ከሚፈልገው ቁጥር ዓይነትና በላይ የሆኑትን ቅርሶችን እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ሌላ ተመሳሳይ ማእከሎች ወይም የትምህርት ተቋማት በቋሚነት ማዛዋወር ወይም መስጠት ነው፡፡

2. **የቅርስነት እሴት ያጡትን ቅርሶች ማስወገድ፡-**

   በመጎዳታቸው ምክንያት ተጠግነው ወደ ቀድሞ ይዞታቸው መመለስ የማይችሉ የቅርስነት እሴት ያጡትን ቅርሶች በመለየት ማስወገድ ማለት ነው፡፡

3. **የስብስብ ማእከል፡**

   የተለያዩ ቅርሶች ተሰባስበው የሚጠበቁበት፣እንክብካቤ የሚደረግበት ፣የሚደራጁበትና ለቀጣይ ጥናትና ምርምር ዝግጁ የሚሆኑበት ክፍል ወይም ማዕከል ነው፡፡

4. **የቴክኒክ ኮሚቴ፡-**

   የሚመለከተው ስብስብ ክፍል ሃላፊ፣ የሚመለከተው ባለሙያ፤ የቅርስ ዶክመንቴሽን ባለሙያ እና የቅርስ ቁጥጥርና ክትትል ባለሙያን ያካተተ ቅርስን ከስብስብ ውስጥ ለማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጡትን ቅርሶች ለማጥናት የተቋቋመ የቴክኒክ ኮሚቴ ነው፡፡

5. **ኮሚቴ፡-**

   ቅርስን ከስብስብ ማእከል ለማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጡ ቅርሶችን ለማሰወገድ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ በተቋሙ ዋና ሀላፊ ሰብሳቢነት የሚመራ ኮሚቴ ነው፡፡

6. <u>የውጭ ባለሙያ፡-</u>

ቅርስን ከስብስብ በማውጣትና በማስወገድ ሂደት አስፈላጊ ሲሆን ለኮሚቴው ሙያዊ አስተያየትና የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ በቅርስ አስተዳደርና አጠባበቅ እውቀት ያለው ባለሙያ ነው፡፡

7. <u>የቅርስ ስብስብ ማእከል ባለሙያ(ኩሬተር)፡-</u>

በስብስብ ማእከሎች ውስጥ የሚገኙ ቅርሶችን የሚንከባከብ፤ ጥናትና ምርምር የሚያደርግና የሚያደራጅ ባለሙያ ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ቅርሶችን ስለማዛወርና ስለማስወገድ</u>

### 4. <u>ቅርስን ከስብስብ ማእከል ስለማዛወር</u>

በስብስብ ማእከሉ ከሚፈልገው ቁጥር በላይ የሆኑትን ቅርሶችን እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ሌላ ተመሳሳይ ማእከሎች ወይም የትምህርት ተቋማት ማዛወር ወይም መስጠት ሲሆን ይህም የሚከናወነው በሚከተሉት ይሆናል፤

1. አትራፊ ላልሆኑ የምርምር ወይም ትምህርት ተቋማት ወይም ድርጅቶች ወይም ሙዚየሞች በስጦታ ወይም በለውጥ ማስተላለፍ፡፡
2. ቅርሱን ወደ ቀድሞ ባለይዞታው መመለስ፤

### 5. <u>ቅርስን ከስብስብ ማእከል የማዛወር መስፈርቶች</u>

1. በስብስብ ማእከሉ ውስጥ ተመሳሳይ ቅርሶች በመኖራቸው ትርፍ ወይም ድግግሞሽ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. የቅርስ ባለይዞታዎች ቅርስን በባለቤትነት ከያዙ፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና የምርምር ተቋማት ቅርሶችን መለዋወጥ አስፈላጊነቱ ሲረጋገጥ፡፡

### 6. <u>የቅርስነት እሴት ያጡትን ቅርሶች ስለማስወገድ</u>

1. በመጎዳታቸው ምክንያት ተጠግነው ወደ ቀድሞ ይዘታቸው መመለስ የማይችሉትን ወይም መረጃው ሙሉ በሙሉ የጠፋ ወይም ከጥቅም ውጪ የሆኑና የቅርስነት እሴት ያጡ ቅርሶችን በቋሚነት ከስብስብ ውጭ ማድረግ ወይም ማስወገድ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት እንዲወገዱ የሚመረጡ ቅርሶች በማቃጠል ወይም በመቅበር ሊወገዱ ይችላሉ፡፡

### 7. <u>የቅርስነት እሴት ያጡትን ቅርሶች የማስወገድ መስፈርቶች</u>

1. በስብስብ ውስጥ ያለ ቅርስ በመጎዳቱ ወይም ተሰብሮ አካሉ በመጉደሉ ሊጠገን የማይችልና የቅርስነት እሴት ያጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. ቅርሱ በተፈጥሮና በሠው ሠራሽ አደጋ ምክንያት በመጎዳቱ ወይም በመበላሸቱ ምክንያት የቅርስነት እሴት ያጣ እና ለሌሎች ቅርሶችና ለሰዎች ደህንነት አደገኛ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

3. በሚደረግ ጥናት የቅርስነት እሴት እንደሌላቸው ሲረጋገጥ፣

## ክፍል ሶስት
## ኮሚቴ ስለማቋቋም

### 8. ቅርሰን ከስብስብ ለማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጡትን ቅርሶች ለማስወገድ ስለሚቋቋም የቴክኒክ ኮሚቴ

1. በስበስብ ክፍሉ ሰብሳቢነት የሚመለከተው ባለሙያ፤የቅርስ ዶክመንቴሽን ባለሙያ እና የቅርስ ቁጥጥርና ክትትል ባለሙያን ያካተተ ቅርስን ከስብስብ ለማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጡትን ቅርሶች ለማስወገድ አጥንቶ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ኃላፊነት ያለው የቴክኒክ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

2. የኮሚቴው አባላት የሚከተሉት ናቸው፡

   1. የስብስብ ክፍሉ ሃላፊ-----------------------------------ሰብሳቢ
   2. የሚመለከተው ስበስብ ክፍል ባለሙያ-------------------አባል
   3. የቅርስ ቁጥጥርና ክትትል ባለሙያ ----------------------አባል
   4. የቅርስ እንክብካቤና ጥገና ባለሙያ----------------------አባል
   5. የቅርስ ዶክመንቴሽን ባለሙያ --------------------- --አባልና ፀሐፊ

### 9. የቴክኒክ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

1. በስብስብ ክፍል ኃላፊዎች ቅርስ ከስብስብ እንዲዛወር ወይም የቅርስነት እሴት ያጡ ቅርሶችን እንዲወገዱ ሃሳብ ሲቀርብለት በመስፈርቶቹ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያረጋግጣል
2. ቅርስ ከስብስብ እንዲዛወር ወይም የቅርስነት እሴት ያጡ ቅርሶች እንዲወገድ የቀረበው ጥያቄ መስፈርቶቹን ያላሟላ ከሆነ ከባለሙያዎቹ ጋር በመወያየት ቅርሶቹ በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፡፡
3. በቅርስ አጠባበቅ ባለሙያ በማስመርመር የቅርስነት እሴት ያጡ ቅርሶች የሚወገድበትን የተሻለ መንገድ ያመቻቻል፤
4. የስብስብ ማዕከሉን አላማና የቅርስ አሰባሰብ እቅድ ወይም ሌሎች ክልላዊና አካባቢያዊ ህጐች ባገናዘበ መልኩ የቅርስነት እሴታቸውን ያጡ ቅርሶች የሚወገዱበትን ምክንያት የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ ከስብስቡ ክፍሉ እንዲቀርብ ያደርጋል፡
5. ከስብስብ የሚዛወሩ ቅርሶች ወይም የሚወገዱ የቅርስነት እሴት ያጡ ቅርሶች ቅርሶችን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን የያዙ የፎቶግራፍና ሌሎች መረጃዎች ጭምር በተሟላ ሁኔታ በስብስብ ክፍሉና በዶክመንቴሽን ክፍሉ መያዝና ለወደፊቱም የሚጠበቁበትና የሚተላለፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

6. ቅርሱን የሰጠው ወገን ያስቀመጣቸው ገደቦች ካሉ የቅርሱን ማህደር በማየት ያረጋግጣል፤

7. ቅርስ ከስብስብ እንዲወጣ ወይም የቅርስነት እሴት ያጣው ቅርስ እንዲወገድ የተሰጠውን የውሳኔ ሀሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ አፅዳቂ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

8. **ለሚመለከታቸው አካላት ቅርሱ ከስብስብ የሚዛወሩበትን ወይም የቅርስነት እሴት ያጡ** ቅርሶች የሚወገድበትን ምክንያት በመገናኛ ብዙሃን እንዲያውቁ ያደርጋል፡

9. በአምስት አመታት ውስጥ ከስብስብ የተዛወሩ ወይም የተወገዱ የቅርስነት እሴት ያጡ ቅርሶችን ዝርዝር የያዘ ሰነድ ተዘጋጅቶ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል እንዲሰራጭ ያደረጋል፡፡

10. በተቋሙ ዋና ሃላፊ ሰብሳቢነት ከቴክኒክ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ቅርስን ከስብስብ የማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጡትን ቅርሶች የማስወገድ ውሳኔ ተመልክቶ የሚያፀድቅ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

## 10. የውሣኔ ሰጪ ኮሚቴ አባላት፡-

1. የተቋሙ ዋና ሃላፊ ------------------------------------------------ሰብሳቢ
2. ከሚመለከተው የሀይማኖት ተቋም ተወካይ-------------------------አባል
3. የቅርሱ ባለይዞታ---------------------------------------------------አባል
4. የቅርስ ባለድርሻ አካላት ተወካይ------------------------------------አባል
5. የቅርስ ቁጥጥርና ክትትል ሃላፊ-------------------------------------አባል
6. ከቅርስ ጋር ተያያዥ ሙያ ያለው የውጭ ባለሙያ-------------------አባል
7. የስብስብ ክፍሉ ሃላፊ --------------------------------------------አባልና ፀሐፊ

## 11. የውሣኔ ሰጪ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት

1. ኮሚቴው ቅርስ ከስብስብ እንዲዛወር ወይም የቅርስነት እሴት ያጣው ቅርስ እንዲወገድ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በመስፈርቱ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፤
2. በኮሚቴው በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚስማማ ከሆነ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል ወይም ያፀድቃል፤
3. በአጠቃላይ ሁሉም አይነት ውሳኔዎችና ለውጦች በቋሚ ማህደሩ ውስጥ ተመዝግበውና ወቅታዊ ተደርገው እንዲቀመጡ ያደርጋል፤

## ክፍል አራት

**12. ልዩ ልዩ**

1. በአጠቃላይ ምትክ የሌላቸው ናሙናዎች፤ በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች፤ የአርኪዎሎጂና ፓሊዮንቶሎጂ ግኝቶች ወይም ቅሪቶች፣ የአሐዝና የምስል ናሙናዎች፣ በማንኛውም ሳይንሳዊና ሙያዊ ህትመቶች ላይ የወጡ ናሙናዎች ሊወገዱ አይገባም፡፡

2. ለሳይንሳዊ ጥናትና ትንተና አስፈላጊ የሆነን የቅርስ ናሙና ሰባብሮ ወይም ፈጭቶ ማጥናት ሲያስፈልግ በሚመለከተው የቅርስ ስብስብ ሀላፊና በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለ፤ሥልጣን ዳይሬክተር ፈቃድ የሚከናወን ሲሆን በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን የማስወገድ መደበኛ አሰራር መከተል ላያስፈልግ ይችላል፡፡

3. ከስብስብ ክፍሉ ከሚዛወር ቅርስ የሚገኝ ማካካሻ ወይም የገንዘብና የቁሳቁስ ስጦታ መዋል ያለበት በስብስብ ማእከሉ የሚገኙ ቅርሶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ዓላማ ብቻ መሆን አለበት፡፡

**13. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ ስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**14. ቅጣት**

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

**15. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የሚመለከተው ስልጣን ያለው አካል ሊያሻሽለው መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**16. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ ------------ ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አሚን አብዱልቃድር**

**የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስትር**

**-----------ቀን/2005 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ፤**